- ወደ ምስተናገድበት ሀገር ስደርስ
- ስለ ስራ ፈቃድና ስለ መኖሪያ ፈቃድ
- ስለ ስራዮ ሁኔታ
- ብታሰር

*በዚህ መፅሃፍ ላይ ያሉትን ምን ማወቅ ይኖርብኛል የሚለው ፅሁፍ ያዘጋጁት በኣረብ ሀገር ላይ በስደተኛ ሰራተኞች ዙሪያ ላይ ጥናታቸውን እያካሄዱ ያሉ በሊባኖስ የሚገኘው የኣሜሪካን ዩኒቨርስቲ የ2010 ተማሪዎችና በኣይ ኤል ኦ(ILO)ላይበ2009 ኦገስት የታተመ ፅሁፍ፡ በሊባኖስ ስለሚኖሩ ስደተኛ ሰራተኞች በጥቂቱ ጥያቄና መልስ ስለሚኖራቸው ነገር ታውቃለህ የሚሉት ናቸው

*ይህንን መፅሓፍ ለማዘጋጀት የገንዘብ እርዳታ ያደረገዉ ፋዉንዴሽን ቱ ኦፕን ሶሳይቲ የተባለዉ ድርት ነዉ

1

# ወደ ምስተናገድበት ሃገር ስደርስ ምን ማወቅ ይኖርብኛል?

### ጠቅላላ የደም  ምርመራ

- አሰሪዮ ጠቅላላ የደም ምርመራ እንዳደርግ ይጠይቀኛል ይህም ምርመራ ኤች አይ ቪና ሳምባን ያጠቃልላል
- የምርመራው ውጤት ፖዘቲቭ ሆኖ ከተገኘ ወዲያው ሃገሩን ለቅቄ ወደ ሃገሬ መመለስ ይኖርብኛል የምመለሰውም በኤጀንሲው ወጪ ነው

### ከመድረሴ ወይም ከደረስኩ በኋላ ለሚፈጠረው እርግዝና

- በገባሁት የጤና ኢንሹራንስ ምርመራ እንዳደርግ እጠየቃለሁ
- አርግዜ ከተገኘሁ የሊባኖስ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ  ሃገሩን ለቅቄ ወደ ሃገሬ መመለስ ይኖርብኛል
  የምመለሰውም በኤጀንሲው ወጪ ነው

### ከአሰሪዮ ጋር ባልስማማ

- ከሶስትወር በፊት ኤጄንስዮን ማሳወቅ አለብኝ
- ኤጄንሲውም አዲስ ቤት ሊቀይርልኝ ይገባል
- ኤጄንሲው ምንም አይነት ውሳኔ ካልወሰደ በሃገሪቱ ለሚገኘው የሃገሬ ኢምባሲ ማሳወቅ ይኖርብኛል
- በፖሊስ እንዳልታሰርና ለሌሎች አደጎች እንዳልጋለጥም መጥፋት የለብኝም

2 - 3

# ስለ ስራና ስለ መኖሪያ ፈቃድ ምን ማወቅ ይኖርብኛል?

- የሊባኖስ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ  ለአሰሪና ለሰራተኛ ስለዋነኛ መብት  የደነገገው መሰረታዊ ደምብ አለ
- አሰሪዮ ውልና ሰነድ የሚፀድቅበት ቢሮ በሚሄድ (ኬቲብ እል አድል) በራሴ ቋንቋ በሊባኖስ ህግ መሰረት ኮንትራቴን ማስፈረም ወይም ማደስ አለበት
- የኮንትራቱም ግዜ 3አመት ሲሆን ይህም በየአመቱ የሚታደስ ነው
- አሰሪዮ የመኖሪያና የስራ ፈቃዴን በራሱ ሙሉ ወጪ የማሰራት ግዴታ አለበት
- ከአሰሪዮ ቤት በምወጣበት ግዜ የግዴታ የመኖሪያና የስራ ፈቃድ ወረቀቴን ኦርጂናል ኮፒውን የግድ ይዤ
- ካልወጣሁ በመንገድ በሚያገኙኝ ፖሊሶች ልታሰር እችላለሁ
- እንዲሁም አሰሪዮ የሁሉንም ወረቀቴ ኮፒ ለጥንቃቄ ሊኖራቸው ይገባል

# ስለ ስራዮ ሁኔታ

### የስራ ሰአት

ይህ የስራ ኮንትራት በሊባኖስ ያሉት ስደተኛ ሰራተኞች የስራ ሁኔታ ማለትም በኮንትራቱ መሰረት ሁሉ የተስማሙበት ነው፡

- በዛ ቢባል በቀን 10ሰአት መስራት አለበት
- ቢየንስ ለ8ሰአት ያህል ማታ የመኝታ ግዜ ሊኖር ይገባል
- የሳምንት እረፍትም ከ24ሰአት ማነስ የለበትም
- ይህም ከአሰሪ ጋር በመስማማትና በመወያየት የሚሆን ነገር መሆን አለበት

## የሚያስፈልጉኝ እነዚህን ነገሮች

- ንፁህና የግሌ ሰፈ ቦታ
- አልጋ ብርድልብስ አንሶላ ትራስ ፎጣላ ሌሎች አስፈላጊ መፀዳጃ ነገሮች
- ለወቅቱ የሚያስፈልጉ ልብሶችና ማስቀመጫ ቦታ
- መደበኛና በቂ ምግብ በየቀኑ
- በአሰሪዮ ወጪ በወር አንድ ግዜ ወደ ቤተሰብ ስልክ መደወል ከዛ በተጨማሪ ግን በራሴ ወጪ መደወል አለብኝ
- ከቤተሰቦች ሲደውሉልኝ ስልክ ጥሪ የመቀበልና መልሼም የመደወል

## ክፍያና ደሞዝ

አለብኝ፡
- በኮንትራቱ መሰረት በወሩ መጨረሻ ሙሉውን ደሞዝ መቀበል
- ደሞዜንም ካሽ ወይም ጥሬ ገንዘብ መቀበል አሊያም አሰሪያ በባንክ በኩል ወደ ሃገሬ እንዲልክልኝ
  ማድረግ
- ይህም ሲደረግ እኔም አሰሪዮም የፈረምንበት ደረሰኝ መጠየቅ
- ካለተከፈለኝ ኢምባሲዮን ወይም ኤጀንስዮን ማሳወቅ



## ቢያመኝ

አሰሪዮን ግዴታ እነዚህን ማቅረብ
- ሃኪም ጋር መውሰድና መድሃኒት መስጠት
- የሊባኖስ ሰራተኛና ማህበራው ጉዳይ ሚኒስተር በሚያዘው መሰረት ትክክለኛ ኢንሹራንስ

* ኢንሹራንሱ በኢንሹራንሱ ደምብ መሰራት በሞት ግዜ የሆስፒታልና የሬሳ መላክያ ሙሉ ወጪ መሸፈን አለበት

* የአይንና የጆሮ ህምናን ግን መሸፈን አይችልም አሰሪ ኮንትራቴ ኢንዳልቀጥል የሚያደርግበት ምክንያት (የሚቆምበት ግዜ)

## አሰሪ ኮንትራቴ እንዳልቀጥል የሚያደርግበት ምክንያት (የሚቆምበት ግዜ)

ከተስማሁ፡
- በተደጋጋሚ አውቅ ስህተት ብሰራ፤ቸል ብል ወይም ብማታ አሰሪዮንና የአሰሪዮን ቤተሰብ ሊጎዳ የሚችል ነገር ባደርግ
- በሊባኖስ ህግ መሰረት ዳኛው እንደሚወስነው የሚወሰድብኝ ቅጣት

* በዚህ አጋጣሚ ወደ ሃገሬ የመመለስ ግቴታ ያለብኝ ሲሆን የመመለሻ ትኬቴን የምከፍለው ራሴው ነኝ

Eኔ ኮንትራቴ Eንዳልቀጥል የሚያደርገኝ ምክንያት (የማቀምበት ግዜ)

- Aሰሪዮ በኮንትራቴን መሰረት ደሞዜን Eስከ 3ወር ተከታታይ ወራቶች ድረስ ባይሰጠኝ
- Aሰሪዮ ወይም ቤተሰቦቹ ወይም ማንም Eቤት ውስጥ የሚኖር፡ ቢመቱኝ ሰብAዊ መብቴን ባለማክበር ያለፈቃዴ ለወሲብ የሚያነሳሳ Eንቅስቃሴ በማድረግ ቢያስገድዱኝ ወይም ቢደፍሩኝ ይህም ወንጀል በሀኪም መረጃ ተደገፎ ለፖሊስና ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስተር የተመዘገበ ወይም የቀረበ ሲሆን
- መስራት ካለብኝና ከAቅሜ በላይ ስራ ብጠየቅ፡ ለምሳሌ ከቤት ውጪ Eንድሰራ ብጠየቅ ወይም መስራት የሌለብኝ ስራ)

* በዚህ ምክንያት በምመለስበት ግዜ የምመለስበት ትኬት Aሰሪዮ የመክፈል ግዴታ Aለበት



4

# ምናልባት ብታሰር ምን ማወቅ ይኖርብኛል?

ፖሊስ ቢያስረኝይህ መብት አለኝ፡

- ለቅርብ ዘመዶችህ ኢምባሲህ ጓደኞችህ ማሳወቅ ወይም ለአስቸኳይ ጉዳይ በዚህ ወረቀት ላይ የተዘረዘሩት ስልኮች ላይ በመደወል ማሳወቅ ይቻላል
- ለማንኛውም አይነት ምትና ስድብ ተገዢ ኣለመሆን
- ከ48ሰአት በላይ አለመታሰር

በየትኛውም እስር ቤት በፖሊስ ቁጥጥር ስር ብውል

ይህ መብት አለኝ፡
- በንፁህና አስተማማኝ ቦታ መሆን
- አልጋ ብርድልብስ አንሶላ ትራስ ፎጣላ ሌሎች አስፈላጊ መፀዳጃ ነገሮች
- ተገቢ ወይም አስፈላጊ ልብስ
- በቂ ምግብ
- ቢያመኝ መድሃኒት
- ከእስርቤቱ ሃላፊ ፍቃድ በመጠየቅ ለቅርብ ዘመዶችህ ኢምባሲህ ጓደኞችህ ማሳወቅ ወይም ለአስቸኳይ ጉዳይ በዚህ ወረቀት ላይ የተዘረዘሩት ስልኮች ላይ በመደወል የሚያስፈልግህን ህጋዊ እርዳታ መጠየቅ

## ለአስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ለመደወል መደበኛና ቀጥታ የስልክ ቁጥሮች (ሆት ላየን)

## ድርጅቶች፡

| ስም | ስልክ ቁጥር |
|---|---|
| ካሪታስ | 01 - 50 25 50 *ext.* 117 **or** 118 |
| የ24ሰአት ኣገልግሎት | 03 - 09 25 38 |
| ካፋ | 01 - 39 22 20 |
| የ24ሰአት ኣገልግሎት | 03 - 01 80 19 |
| ሪስታርት | 01 - 38 53 58 |

## ኤምባሲዎች፡

| ሃገር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|
| ፊሊፒን | 01 - 21 20 02<br>01 - 21 20 03 |
| ስሪላንካ | 05 - 95 47 63<br>05 - 95 47 66<br>05 - 92 47 65<br>05 - 92 46 02 |
| ኔፓል | 01 - 38 66 90<br>01 - 39 60 02 |
| ኢትዮጵያ | 01 - 38 87 86<br>01 - 38 89 23 |